የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የይ/መ/ቁ 211445

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሾመ ሽፈራው

ኑረዲን ከድር

ሀብታሙ እርቅይሁን

ይግባኝ ባይ፡- ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ተወካይ ማዕከል አየነው ቀርበዋል፡፡

መልስ ሰጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነ/ፈጂ አብድሮ ታደሰ እና አቶ ወንጌል አባቴ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው የቀረበውን የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው ይግባኝ ባይ ያቀረበለትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ የሰጠው ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም ሲሆን ይግባኝ ባይ በቦርዱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበው ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) ላይ እንደተመለከተው የድምጽ ቆጠራና ውጤት አስመልክቶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት በቦርዱ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአስር ቀናት ውስጥ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ይግባኝ ባይ በአዋጁ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ አልቻልኩም በማለት ባቀረበው አቤቱታ የጠቀሳቸው ምክንያቶች ውሳኔ ሌሎች ፓርቲዎችን አስመልክቶ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ውሳኔው የማስረጃ እና የዳኛው ሃተታ እንዲሁም በየምርጫ ክልሉ ያቀረባቸው ምስክሮች ሙሉ ቃል የሰነድ የፎቶ እና የድምጽ ግልባጭ ተሟልቶ እንዲሰጡት የጠየቀ ቢሆንም ቦርዱ ምላሽ ያልሰጠው መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ በዚህም ላይ መልስ ሰጭ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 3/12/2013

Federal Supreme Court
The Federal Democratic Republic of Ethiopia

አስተያየት እንዲያቀርብ በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት የይግባኝ ባይ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር አቤቱታው ውድቅ እንዲያደረግ በማለት ምልሽ ሰጥቷል፡፡

በበኩላችን እደተመለከትነው ቦርዱ የይግባኝ ባይን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ መስጠቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ለይግባኝ ባይ የፃፈው ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ቀን ቦርድ ውሳኔ የሰጠበት ቀን እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይግባኝ ባይ የቦርዱ ውሳኔ የደረሰኝ ሐምሌ 12 ቀን ነው በማለት ይከራከራል፡፡ በአዋጁ የተመለከተው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን እንጂ ውሳኔ ለአቤቱታ አቅራቢው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ አያሳይም፡፡ ያም ሆኖ የቦርዱ ውሳኔ ለይግባኝ ባይ የተሰጠው ይግባኝ ባይ እንደሚለው ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ሳይሆን ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም ስለመሆኑ መልስ ሰጭ ካቀረበው የደብዳቤ መቀበያ ደረሰኝ ሞዴል 51 ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አላለፈም በሚል ይግባኝ ባይ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመቀጠል መታየት ያለበት ነጥብ ይግባኝ ባይ የይግባኝ ማቅረቢያ አቤቱታውን በአዋጅ በተመለከተው ጊዜ ሳያይቀርብ የቀረው በበቂ ምክንያት መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢ ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ አቅራቢ የይግባኝ ማስፈቀጃ ሊያቀርብ የሚችልበት ሥርዓት በአዋጅ ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ማስፈቀጃ ሥርዓትን አስመልክቶ በፍ/ብ/ስ/ስርዓት ህጉ አንቀጽ 324 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህም ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስርዓት ህጉ አንቀጽ 326 ላይ ከተመለከተው ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረው ለማስፈቀጃው መሰረት የሆነው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከት ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ ሐተታ የሌለበት መሆኑ የምስክሮች ሙሉ ቃል ጨምሮ ሌሎች የተለያዩ የሰነድ የፎቶ እና የድምጽ ግልባጭ በመልስ ሰጭ አለመሰጠቱ ይግባኝ ባይ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔ ላይ በአዋጁ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኙን አእንዲያቀርብ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ባይ ያቀረበው ይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም/ቶ